# Learning by Ear 2013

**«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–«መዘዙን መቀበል»**

EPISODE 5: «በህልሜ»

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, ዳንኤልiel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: ቅዱስ DREAMS ABOUT LABORIA**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ብሩክ (M, 8)**
- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **SUPERVISOR (M, 50)**
- **3 BOYS (M, 10-15)**

**SCENE 2: AT THE አቶ ጃለታS'**

- **ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 35)**
- **አቶ ጃለታ (M, 45)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

**SCENE 3: IN ዳንኤል'S ROOM**

- **ዳንኤል (M, 16)**
- **በለጠ (M, 16)**

**SCENE 4: AT THE POLICE STATION**

- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**

- *ፖሊስ ሙሉጌታ*(M, 45)

**INTRO**

## 1. NARRATOR:

**ይህ«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ—«መዘዙን መቀበል» የሚለው የሬዲዮ ድራማ ነው። ወጣቶቹ ብዙ ፈተናዎች እየገጠማቸው ነው፤ 15 አመቷ ምህረት ሙላቱ ከክፍል ጓደኛዋ ዳንኤል ጋ ለግብረ ስጋ ግንኙነት ከቸኮለች በኋላ ወዲያው አርግዛለች። ዳንኤልን ግን ይህ ዜና ፍፁም አላስደሰተውም እናም ፅንሱን እንድታስወርድ ይፈልጋል።**

## 2. EPISODE 4, LINES 94 - 96:

*ዳንኤል: ያውልሽ ገንዘቡ። ፅንሱን አስወርጂና ሰላሜን ስጪኝ ምህረት። የምልሽ ይገባሻል? (…)*

*ምህረት: ገንዘብህን ልትወስድ ትችላለህ። አልፈልገውም።*

*ዳንኤል: ጥሩ! እንግዲያውስ እዛው ቆሻሻ ውስጥ ተይው። ግን ነገሮች ሲባባሱ እያላዘንሽ እኔ ጋ እንዳትመጪ።*

## 3. NARRATOR

**የክፍል ጓደኛቸው ንጉሴ ስለዚህ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። ከምህረት ፍቅር ይዞታል ግን እሷ አልፈልግህም ብለዋለች።በዚህም የተነሳ እፅ መውሰድ ጀምሯል። በሌላ በኩል የምህረት አባት አቶ ሙላቱ በእስር ላይ ሳሉ ባለቤታቸው ወደ ፖለቲከኛው አቶ መኩሪያ ቤት ሄደው አዲስ ነገር አግኝተዋል።**

## 4. EPISODE 3, LINES 49 - 50:

*ወ/ሮ ሉሊት: ሙላቱ ልጄን የሸጠለት ሰው አንተ ነህ? ልጄን መልሰህ ስጠኝ።*

***MUKARABA:*** *እሚ! ይህ ነው የሚይባል ገንዘብ ነው ለህፃኗ የከፈልኩት። በዛ ላይ ያሉሽን ልጆች እንኳን የምታበያቸው የለሽም።*

## 5. NARRATOR:

የምህረት እናት ወ/ሮ ሉሊት የሰሙትን ማመን አቅቷቸዋል። መንታ ልጆቻቸውን ቅዱስ እና ብሩክን ማጣታቸው ሲያብከነክናቸው መክረሙ ካበቃ ብዙም አልቆየ።ልጆቹ ጎረቤት ሀገር ላቦሪያ አክስታቸው ወ/ሮ ለምለም ዘንድ እንዲያድጉ ነበር የተላኩት። ሆኖም በእራሳቸው ተመልሰው መጥተዋል። እዛ ሳሉ ምን ገጥሟቸው ይሆን? የዛሬው ጭውውት « በህልሜ» ይሰኛል። እስቲ ምህረት እና ወንድሞቿ ቤት ሳሉ እናግኛቸው። …

## <u>SCENE 1: ቅዱስ DREAMS ABOUT LABORIA</u>

## 6. ATMO: NIGHT IN THE SLUMS, INDOORS

**7. ምህረት:** **(to herself)** ወይኔ! መተኛትእንኳን አልቻልኩም! ዳንኤል ገንዘቡን ሲወረውርልኝ እንዴት አስቀያሚ ፊት እኮ እንዳሳየኝ። ከዳንኤል ድጋሚ ገንዘብ መቀበሉ ለመሆኑ ልክ ነበር? ግን እዛ ጭቃ ላይ ትቸው ልሄድ አልችልም ነበር። …ሌላ ምን ማድረግ እችል ነበር… ሆዴ ውስጥ ልጅ እያደገ መሆኑን እስካሁን ማመን አልቻልኩም። …. ምናልባት ትዕግስት እና እሱ ልክ ይሆናሉ። ያለው ብቸኛ አማራጭ ይሄ ብቻ ነው።

## 8. SFX: ምህረት TURNING OVER

**9. ምህረት:** **(deep breath)** እንደወንድሞቼ ትንሽ ለመተኛት ብሞክር ሳይሻል አይቀርም። ቅዱስ ድብን ያለ እንቅልፍ ወስዶታል… ምን እያለመ ይሆን…

**10. ቅዱስ:** **BREATHING DEEPLY WHILE ASLEEP, MAKES NOISES OF FEELING UNCOMFORTABLE / WHINES IN HIS SLEEP**

**11. SFX: ECHO-EFFECT FOR ALL VOICES AND SOUNDS IN DREAM**

**12. SFX: FADE IN MINE ATMO, HAMMERS HITTING HARD SURFACE (VERY RHYTHMICALLY), MACHINES WHIRRING**

**13. SUPERVISOR:** **(unfriendly)** ስማ! አንተ ልጅ! እነሱን አለቶች ተጠንቀቅ። እዚህ ዋሻው እናታችን ላይ ተደርምሶ ሁላችንም እንድናልቅ ፈልገሃል?

**14. ቅዱስ:** **(grumpy)** ግን በጣም እርቦኛል። በዛ ላይ እጆቼ እያመመኝ ነው።

**15. SUPERVISOR:** ምን ይላል ይሄ፤ እኛም ተርበናል ባክህ ፣ እጆቻችንንም እያመመን ነው አይደለም እንዴ?

**16. BOYS:** **(Scattered tired voices)** አዎ!

***KW BEGIN***

**17. SUPERVISOR:** አትሰሙኝም…

**18. BOYS:** **(Louder but still tired)** አዎ!

**19. SUPERVISOR:** ሰማህ? ሁሉንም አርቧቸዋል። ግን ለመብላት መስራት አለባቸው። አንተም ለመብላት ከፈለክ ወደ ስራህ ተመለስ። ካለበለዚያ ዛሬ ሌሊት አንዲት የሚቀመስ አታገኛትም።

**20. ብሩክ :** ግን አለቃ ወንድሜ ቅዱስ --

**21. SUPERVISOR:** አቶ አለቃ! ገብቶሀል? የምትጠራኝ አቶ አለቃ እያልክ ነው።ገባህ?

**22. ብሩክ :** እሺ አቶ አለቃ። ይቅርታ።

***KW END***

**23. SUPERVISOR:** አንተ እና ወንድምህ ይሄ ማልጎምጎማችሁለመጨረሻ ጊዜ ቢሆን ይበጃልእንደ ትናንትናው ልጅ መቀጣት ትፈልጋላችሁ?

**24. ብሩክ :** አንፈልግም አቶ አለቃ!

**25. ቅዱስ:** አባክዎን አይምቱን! **(crying)** ወደ ቤቴ መሄድ እፈልጋለሁ። እማዬን እፈልጋለሁ። እማ! እማዬ! እማ! **(continues to cry for his mum)**

**26. SFX: MINE ATMO AND SOUNDS FADE OUT WHILE** ቅዱስ **CONTINUES CRYING FOR HIS MUM, ECHO STOPS**

**27. SFX: NIGHT ATMO AT TANDIKA FADE IN**

**28. ቅዱስ:** እማ! እማዬ! እማ!

**29. SFX: STEPS -** ወ/ሮ ሉሊት **APPROACHING**

**30. SFX: RUSTLING OF CLOTHES AS SHE CUDDLES HIM**

**31.** ወ/ሮ ሉሊት: ወይ ጉዴ! ና ወደዚህ ቅዱስ። የኔ ውድ አይዞህ። በህልምህ ነው። ልጄ መጥፎ ህልም ነበር።

**32.** ቅዱስ: **(cries)** እማ ያ ሰውዬ በጣም መጥፎ ሰው ነው። ብዙ ሲያሰራን ነበር። በዛ ላይ ሊመታን ፈልጎ ነበር።

**33.** ወ/ሮ ሉሊት: እውይ ልጄን! አይዞህ አሁን ምንም አትሆን፤ እናታችሁ አጠገባችሁ ናት። ልጄን ምንድን ነው ያደረጉህ? አክስትህ ለምለም ይህ ሁሉ ሲሆን የት ነበረች?

**34.** ቅዱስ: ሰውየው ጋ ማዕድን ማውጫው ውስጥ ነው የተወችን።

**35.** ብሩክ : **(sleepily, coughs)** ቅዱስ? አሁን ምንም አንሆንም…

**36.** ወ/ሮ ሉሊት: ልክ ነው። እዚህ ምንም አትሆኑም። የሆነውን ሁሉ ልትነግሩኝ ትችላላችሁ።

**37.** ብሩክ : ግን አክስቴ ለምለም እንዳትነግሩ --

**38.** ወ/ሮ ሉሊት: እሽሽሽ ብሩክ። ለምለም እዚህ የለችም። እኔ እጠብቃችኋለሁ። የሆነውን ነገር በሙሉ ነገ ትነግሩኛላችሁ እሺ?

**39.** ብሩክ /**KADA:** እሺ እማዬ!

**40.** ወ/ሮ ሉሊት: አሁን በሉ ተኙ። እናታችሁ አለች እሺ።

**41. MUSICAL INTERLUDE (soft music)**

**SCENE 2: AT THE አቶ ጃለታS'**

**42. SFX: Programme on TV**

**43. SFX: MORNING ATMO AT THE አቶ ጃለታS'**

**44.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(Hums to herself)**

**45. SFX: TABLE BEING SET**

***KW BEGIN***

**46.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ለምንድን ነው ቁርስ ሊበሉ የማይመጡት? **(shouts)** ቁርስ ደርሷል እኮ ነው የምላችሁ። ንጉሴ! ጃለታ! ዛሬ ማንኛችሁም መብላት አትፈልጉም?

**47. SFX: FOOTSTEPS COMING DOWN THE STAIRS**

**48.** አቶ ጃለታ: እንደምን አደርሽ የኔ ውድ?

**49.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ምነው በስንት ጥሪ መጣህ!

**50. SFX: አቶ ጃለታ SITS DOWN**

**51.** አቶ ጃለታ: **(pleasantly)** በእውነት መነጫነጭ ደስ ይልሻል ልበል የንጉሴ እናት?

**52.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(offended)** እየተነጫነጭኩ አይደለም። ቁርስ ደርሷል ነው ያልኩህ።

**53.** አቶ ጃለታ: **(resigned)** ኡፍ! ታውቂያለሽ? አርፈን እንብላበት **(hesitates)** ንጉሴ የታል? አልተነሳም እንዴ? 4 ሰዓት እኮ ሆኗል። ለወትሮው ቅዳሜና እሁድ እንኳን በጠዋት ነበር የሚነሳው።

**54.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ከግማሽ ሰዓት በፊት ወደመታጠቢያ ቤት ሲገባ አይቸዋለሁ። እስካሁን ከዛ አልወጣም።

**55.** አቶ ጃለታ: ምንድን ነው ይሄን ሰሞን ይሄ ልጅ እና መታጠቢያ ቤት? እዛው መኖር ጀመረ እንዴ?

**56.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ጃለታ ልጅህ እየጎረመሰ ነው። ምናልባት እራሱን እያሽሞነሞነ ይሆናል። እንግዲህ እንዲት የወደዳት ልጅ ትኖራለች።

***KW END***

**57. SFX: FOOTSEPS AS ንጉሴ WALKS IN**

**58.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: እሰይ ይሄው መጣ ቆንጅዬው ልኡል። እንዴት አደርክ ንጉስዬ ። መልካም ማለዳ

**59.** ንጉሴ: **(flatly)** እንደሱ ካልሽ።

**60. SFX: ንጉሴ SITS DOWN, CHAIR PULLED OUT**

**61.** አቶ ጃለታ: እንደሱ ካልሽ ስትል ምን ማለትህ ነው? እናትህ እኮ እንደምን አደርክ፤ መልካም ማለዳ ነው ያለችህ። እና ማለት የምትችለው« እንደሱ ካልሽ» ብቻ ነው?

**62.** ንጉሴ: እንግዲህ እሷ ጥሩ አድራ ይሆናል… ለኔ ግን ጥሩ አልነበረም።

**63.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ለምን የኔ ልጅ?

**64.** ንጉሴ: እሱ አያገባሽም።

**65.** አቶ ጃለታ: አንተ ደፋር! ለእናትህ እንደዚህ አይነት መልስ አትሰጥ! **(slaps him)**

**66. SFX: SLAP ON FACE**

**67.** ንጉሴ: **(yelps)** የምትችለው ነገር ቢኖር እኔ ላይ መጮህ እና መማታት ብቻ ነው!

**68. SFX: CUTLERY THROWN ON PLATE**

**69. SFX: ንጉሴ STANDS UP, FAST FOOTSTEPS**

**70. ንጉሴ: WALKS AWAY SNIFFLING**

**71.** አቶ ጃለታ: **(authoritarian)** ንጉሴ ና! ተመለስ ብያለሁ።....

**72. SFX: DOOR OPENED AND BANGED**

**73.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(shouts)** ንጉሴ ና የኔ ልጅ! የት ነው የምትሄደው? **(to** አቶ ጃለታ**)** በጥፊ መምታት አልነበረብህም!

**74.** አቶ ጃለታ: በቃሽ! ይሄን ልጅ እያጨማለቅሽው ነው ያለሽው የንጉሴ እናት። ለምን ልክ እንደ ህፃን ሽንት ጨርቅ አታስሪለትም።

**75.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(gives in)** ጥሩ። እንደፈለክ ማለት ትችላለህ፤ እሺ ይቅርታ። አሁን ቁርሳችንን እንብላ።

**76.** አቶ ጃለታ: የምግብ ፍላጎቴ ሁላ ጠፍቷል። ወደእዛ ልሂድና ገላዬን ልታጠብ!

**77. SFX: FOOTSTEPS AS አቶ ጃለታ LEAVES**

**78. MUSICAL INTERLUDE**

## <u>SCENE 3: IN ዳንኤል’S ROOM</u>

**79. SFX: BONGO ACADEMY, INSIDE ዳንኤል’S ROOM, DAYTIME (WEEKEND)**

**80. SFX: SOFT MUSIC HEARD THROUGH HEADPHONES (LBE-SONG)**

**81. ዳንኤል:** **(Raps/sings along loudly to music on headphones)**

**82. SFX: KNOCK ON DOOR**

**83. በለጠ:** **(from outside)** ዳንኤል? ዳንኤል!

**84. ዳንኤል:** **(Doesn’t hear, continues to rap/sing)**

**85. SFX: KNOCK ON DOOR**

**86. SFX: DOOR OPENS**

**87. SFX: FOOTSTEPS ENTERING**

**88. በለጠ:** **(loudly)** ዳንኤል ልትቀንሰው ትችላለህ?

**89. ዳንኤል:** **(loudly)** በለጠ! ምንድን ነው ያልከው?

**90. በለጠ:** ማዳመጫውን ከጆሮህ ላይ አንሳው

**91. ዳንኤል:** እ፤ እሺ።...

**92. SFX: MUSIC GOES SILENT**

***KW BEGIN***

**93. ዳንኤል:** **(Lower voice)** ይቅርታ በለጠ ምን ነበር ያልከው?

**94. በለጠ:** ድምፁን ቀንስ! ርዕሰ መምህርት ሰብለ ልትሰማ እና ኮምፒተርህን ልትነጥቅህ ትችላለች። ከዛ እንዴት ፊልማችንን ልናይ ነው?

**95. ዳንኤል:** ይጮህ ነበር እንዴ?

**96. በለጠ:** **(laughs)** ትቀልዳለህ እንዴ? እወራረዳለሁ ዘበኛው እንኳን የትኛውን ዘፈን ማዳመጥ እንደምትወድ ያውቃል።

***KW END***

**97. ዳንኤል:** ትንሽ ስለጨነቀኝ እኮ ነው። ለዛ ነው።

**98. በለጠ:** መጨነቅ? ከምህረት ጋ በተያያዘ ነው? ምን አዲስ ነገር አለ?

**99. SFX: ዳንኤል’S CELLPHONE RINGING**

**100. ዳንኤል:** ትናንት ታንዲካ ድረስ ተከትያት ሄድኩ እና ገንዘብ ሰጠኋት።

**101. በለጠ:** ከዛስ?

**102. ዳንኤል:** ገንዘቡን  እንኳን ትውሰድ አትውሰድ አላውቅም።  እኔ ላይ ተቆጥታ ስትጮህ ነበር።

**103. በለጠ:** ስማ  ዳንኤል ስልኩን ማንሳት አትፈልግም? አልማዝ ይላል…

**104. ዳንኤል:** **(stressed)** ተወው ባክህ… አሁን አላነሳሁም። ምናልባት በኋላ እደውልላታለሁ።

**105. በለጠ:** አልማዝ ማናት? ያልነገርከኝ ምስጥር አለ እንዴ?

**106. ዳንኤል:** ተዋት ባክህ። እም ብላ ነው።

**107. SFX: CELLPHONE STOPS RINGING**

**108. ዳንኤል:** **(sighs)** በለጠ በእውነት ነው የምልህ የምህረትን ጉዳይ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም።…

**109. በለጠ:** ታውቃለህ ! ላለፉትን ጊዜያት በጣም ነው ፊት የነሳሃት።  አንዳንዴ ሴቶች ከኛ የሚፈልጉት ጥሩ ሆነን እንድናናግራቸው ነው።

**110. ዳንኤል:** ምን ማለትህ ነው?

**111.** **በለጠ:** ይኸውልህማድረግ ያለብህ... **(fade out)**

**112. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 4: AT THE POLICE STATION

**113. ATMO: POLICE STATION**

**114.** ወ/ሮ ሉሊት: ይቅርታ ፖሊስ! ወ/ሮ ሉሊት እባላለሁ። በተሰረቀው ልጄ ምክንያት ነው የመጣሁት።

**115. OFFICER** ፖሊስ ሙሉጌታ: አንቺ ነሽ የምክር ቤት አባል መኩሪያን የከሰሽቸው?

**116.** ወ/ሮ ሉሊት: አዎ! ፖሊስ። ልጄ እንዴት ናት? እባክዎን ላያት እችላለሁ?

**117.** ፖሊስ ሙሉጌታ: እኛ ጋ ምንም ልጆች የሉምም። **(hesitant)** እንደሚመስለኝ ከማህበራዊ ጉዳይ ተመልካቾች ጋ ናት። በኋላ እዚህ ቃል ለመስጠትይመጣሉ።

**118.** ወ/ሮ ሉሊት: ምንድን ነው የሚሰጡትት?

**119.** ፖሊስ ሙሉጌታ: እሱ የፓሊስ ስራ ነው።

**120.** ወ/ሮ ሉሊት: ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል እስኪመጡ?

**121.** ፖሊስ ሙሉጌታ: ሴትዮ። ስራ እያስፈታሽኝ እኮ ነው። እንደ ሌሎቹ ሰዎች እዛጋ ተቀመጪ. እና ጠብቂ። ስራ ላይ እንደሆንኩ ይታይሻል?

***KW BEGIN***

**122.** **ወ/ሮ ሉሊት:** **(desperately)** የራሴን ልጅ ለማየት እንዴት እንደዚህ ከባድ ይሆናል? ምናል ቢረዱኝ?

**123.** **ፖሊስ ሙሉጌታ:** **(not amused)** እና አሁን ስራችንን እንዴት ማከናወን እንዳለብን ልትነግሪን ነው? ፖሊስ መሆን ትፈልጊያለሽ? **(sarcastic)** ጥሩ - ታዲያ ለምን እዚህ እኔ ጋ መጥተሽ ተቀምጠሽ ስራዬን አትሰሪም።

**124. SFX: DESK PUSHED BACK AS HE STANDS**

**125.** **ወ/ሮ ሉሊት:** ግን…

**126.** **ፖሊስ ሙሉጌታ:** ነይ እንጂ ምን ትጠብቂያለሽ? ፖሊስ እኮ ብትሆኚ ይሻላል

**127.** **ወ/ሮ ሉሊት:** እኔ… እኔ እኮ እንደሱ ማለቴ --

**128.** **ፖሊስ ሙሉጌታ:** ጥሩ። አፍሽን ዘግተሽ ስራችንን ብታሰሪን ይሻላል።

**129.** **ወ/ሮ ሉሊት:** ይቅርታ ፖሊስ

***KW END***

**130.** **ፖሊስ ሙሉጌታ:** **(clicks his tongue)** እንደ ሌሎቹ ሰዎች እዛ ጋ ተቀመጭ እና ጠብቂ።

**131.** **ወ/ሮ ሉሊት:** እሺ ጌታዬ!

**132. SFX: FOOTSTEPS AS ወ/ሮ ሉሊት GOES, STOPS**

**133.** **ወ/ሮ ሉሊት:** **(calls)** ፖሊስ?

**134.** **ፖሊስ ሙሉጌታ:** **(agitated, from afar)** አሁን ደግሞ ምንድን ነው?

**135.** ወ/ሮ ሉሊት: ጥሩ እሺ እባክዎን ባለቤቴን አቶ ሙላቱን ማየት እችላለሁ?

**136.** ፖሊስ ሙሉጌታ: ታሳሪዎቹን መጎብኘት የሚቻልበት ሰዓት እስኪደርስ መጠበቅ አለብሽ። ባለቤትሽ በዘረፋ ወንጀል ተጠያቂ ሆኗል። እዚሁ ሳይሰነባብት የሚቀር አይመስለኝም።

## 137. OUTRO - NARRATOR

እንግዲህ ለዛሬ ያልነው የእስካሁኑ ነበር። ወ/ሮ ሉሊት ለህፃን ልጃቸው ትግላቸውን ይቀጥሉ ይሆን? እነ ምህረት ንጉሴ እና ዳንኤልስ? ታሪካቸው እንዴት እንደሚቀጥል ማወቅ ከፈለጋችሁ በሚቀጥለው ጊዜ ጠብቃችሁ መከታተላችሁን እንዳትረሱ። በነገራችን ላይ ዳንኤልን በስልክ ለማግኘት የምትሞክረዋ ልጅ ማን ትሆን? ስሟ አልማዝ ነው አይደል? ለምን እንደደወለች እና ስለሀገራቸው ላቦሪያ ሁኔታ ለዳንኤል ምን ልትለው ፈልጋ እንደነበር ማወቅ ከፈለጋችሁ የሷን አዲስ የቪዲዮ ዘገባ ተከታተሉ።የድረ ገፁ አድራሻችን: dw.de/lbe ነው። ደህና ሁኑ!